# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት

## አቅራቢዎች



# የነሕሚያ ታላቁ ግንብ።

ጸሐፊው: Edward Hughes

ምሣሌ አቅራቢው: Jonathan Hay

ያሻሻለው (አሻሽሎ የጻፈው): Mary-Anne S.

የተተረጎመው: Zemendale Translation Service
email: zemendale@gmail.com
Po Box 32155, Addis Ababa, Ethiopia

አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org

©2024 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፦ ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል
ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።

ፋርስ ፣ ታላቁ መንግስት ፣ ዓለምን
ገዛ፡፡ ንጉስ አርጠክስስም ፋርስን
ገዛ፡፡ ይሄም እርሱን የአለማችን
ታላቁ መሪ አደረገው፡፡ ከንጉሱ
እጅግ ጠቃሚ አጋዥ ሰዎቸ መካከል
አንደኛው ነህምያ ነበረ፡፡ ስራውም
ንጉሱን ከተመረዘ ምግብ ለመከላከል
፣ ለንጉሱ ይቀርቡ የነበሩትን ምግቦች
መቅመስ ነበረ፡፡



አንድ ቀን ፣ ነህሚያ ወደ ንጉሱ ፊት እጅግ ባዘነ ገጽታ ሆኖ ቀረበ፡፡ ንጉሱም የተፈጠረው ነገር ምን እንደሆነ ማወቅ ፈለገ፡፡ “ንጉስ ሆይ ፣ ለዘላለም ኑር፡፡” ነህምያም አለው ፣ “አባቶቼ የሚኖሩባት ከተማ ፈርሳ በሮቿም ተቃጥለዋል፡፡” ነህምያ ስለ ኢየሩሳሌም እያወራ ነበረ ፤ ከብዙ አመታት በፊት በጦርነት ምክንያት ፈራርሳ ነበረ፡፡



ንጉስ አርጤክስስም እንዲህ ብሎ ጠየቀ ፣ “ምን እንዲሆን ትወዳለህ;” ነህሚያም መለሰ ፣ “ወደ ኢየሩሳሌም ልሂድና ደግሜ ልገንባው፡፡” ንጉስ አርጤክስስም በመልካምነት ተስማማ፡፡ በሚጓዝበትም ወቅት እንዲጠበቅ ፣ ደብዳቤን ጽፎ ሰጠው፡፡



ንጉስም እጅግ ብዙ አድርጎ ረዳው፡፡ የንጉሱን ደን ለሚጠብቀው ለአሳፍ ደብዳቤን እንዲሰጠው ብሎ በነሕምያ እጅ ላከለት፡፡ ከተማይቱንም ይገነባ ዘንድ እንዲቻለው አሳፍ በቂ የሆነ አጠና እንዲሰጠው በንጉሱ ታዘዘ፡፡



ነሕምያም በኢየሩሳሌም ሲደርስ ፣ የከተማይቱን ሹማምንት ሰብስቦ እንዲህ አላቸው ፣ “ እኛ እዚህ እጅግ እየተቸገርን ነው ፤ ከተማይቱ በመፈራረስ እንዲሁም በሮቿም በመቃጠል ላይ ናቸው ፡፡ ደግመን መገንባትን እንጀምር፡፡” ንጉስ አርጤክሳስ እንደፈቀደ እና ከሁሉም በላይ ደግሞ እግዚአብሔር ከእነርሱጋ እንደሆነ ነገራቸው፡፡



የነሕምያ እምነትና ናፍቆት ሰዎቹን እጅግ አስደነቃቸው፡፡ ተስማምተውም እንዲህ አሉ ፤ “እንገንባው” ነሕምያም የቱኛው ቤተሰብ የቱኛውን የቅጥሩን ክፈል መጠገን እንዳለበት ነገራቸው፡፡



ነገር ግን ፣ ሁሉም ቅጥሩን ለመገንባት ፈቃደኛ አልነበሩም፡፡ ሰንበላጥ የሚባል ሰው እንዲሁም ጦቢያና ጌሳም የሚባሉ የእርሱ ሁለት ጓደኞች አይሁዳዊያን አልነበሩምና ቅጥሩ እንዲሰራ አይፈልጉም ነበረ፡፡



ስራው እንቀጠለ ፣ ሰንበላጥ እጅግ ተቆጣ ፡፡ እርሱና ጓደኞቹ በአይሁዳዊያኑ ላይ መሳለቅ ጀመሩ፡፡ ጦቢያም ፣ “ያንን ደካማ ቅጥር ሰርተው ሲጨርሱ ፣ ቀበሮዎቹ ሲወጡበት ይወድቃል፡፡” ነሕምያም ምላሽን አልሰጠም ነበረ፡፡ በምትኩ ፣ እግዚአብሔር ከእነርሱጋ እንዲሰራ ጸለዩ፡፡



የእነርሱ የስድብ ቀልድ ምንም አይነት ውጤት አልነበረውም ፤ ሊያመጡ ከሚችሉት ችግር በላይ ለማድረግ በኢየሩሳሌም ላይ ለመነሳት ተባብረው አሴሩ፡፡ በተጨማሪም ፣ ነህምያ የእግዚአብሔርን ረድኤት ለመነ፡፡ በድንገተኛ ነገር እንዳይወስዱ ፣ ቀንና ሌሊት የሚጠብቁ ጠባቂዎችን አኖሩ፡፡



አይሁዳዊያኑ በጣም ይሰሩ ነበር ፤
እጅግ ይደክማቸውም ነበረ፡፡
አንዳንዶቹ በስራ ላይ እያሉ
ጠላቶቻቸው መጥተው ሊገዱሏቸው
እንደሚችሉ እያሰቡ ይፈሩ ነበር፡፡
ቢሆንም ፣ ነህምያ ስራውን
አያቆምም ነበረ፡፡ በሰራተኞቹ ዙሪያ
ጠባቂ አኖረ እና እግዚአብሔር
ከእነርሱጋ እንዳለ አሳሰባቸው ፤
እግዚአብሔር ከጠላቶቻቸው ይልቅ
ኃያል እንደሆነም ነገራቸው፡፡



ነሕምያ መልካም
ምሳሌ ለመሆን
ሞከረ፡፡

ንጉስ አርጤክስስ በኢየሩሳሌም
ላይ ገዢ አድርጎት ከሰዎች ላይ
ምግብና ገንዘብ እንዲቀበል
መብት ሰጥቶት ነበረ ፤ ነገር ግን
ነሕምያ ይሔንን አላደረገም፡፡
ቅጥሩን ሲሰሩት አብሯቸው
በመሆን ጠንክሮ ይሰራ ነበረ፡፡
ምግብ ለመግዛትም የራሱን
ገንዘብ ይቀበል
ነበረ፡፡



በመጨረሻም ፣ ሰዎቹ ቅጥሩን ሰርተው ጨረሱ ፤ በሩ ብቻ በዋናው መግቢያ በኩል መቀመጥ ነበረበት ። ሰንበላጥ ፣ ጌሳም እና ጦቢያ በቅጥሩ ዙሪያ ምንም ክፍተት እንደሌለ ባወቁ ሰዓት ፣ ነሕምያን ለመጉዳት አሰቡ።



ኦኖ በሚባል ስፍራ ለማግኘት ፈልገው ለነሕምያ ደብዳቤን ላከላቸው፡፡ ነሕምያ ግን ሊያጠቁት አስበው ይሄንን እንዳደረጉ በማሰብ ሊጎዱት እንደሆነ ቀድሞ አወቀ፡፡ ስራውን ትቶ እነርሱን ማግኘት እንደማይችል ሊነግራቸው ደብዳቤን ላከላቸው፡፡




በስተመጨረሻም ቅጥሩ
ተሰርቶ አለቀ ፤ እርሱንም
ለመጠበቅ ነሕምያ
ጠባቂዎችን አኖረ፡፡
ቅጥሮቹ
ጸሐይ እስኪወጣ ድረስ ክፍት ሆነው
እንዳይቀሩ የሚልን ትዕዛዝ አወጣ፡፡
በምሽት ጊዜ ፣ እንዲዘጉ አዘዘ፡፡

አሁን ከተማይቱ ሰላማዊ ሆነች ፤ ከተለያየ ስፍራ ይመጡ የነበሩ የአይሁድ ምርኮኞች ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ፡፡ በተለያዩ እንቅፋቶች መካከል ፣ ነሕምያም እግዚአብሔር ይሰራው ዘንድ የሰጠውን ስራ በማጠናቀቁ ደስተኛ ሳይሆን አልቀረም፡፡

በኢየሩሳሌምም ቆይቶ ሰዎች ሁሉ እግዚአብሔርን እንዲታዘዙ አገዛቸው ፡፡



የነሕሚያ ታላቁ ግንብ፡፡

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሐር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ነህምያ

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

# መጨረሻ

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው። ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16